# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ

## በረቂቅ ብሔራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማእቀፍ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚካሄድ ምክክር

ጥር 2016 ዓ.ም

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

# ክፍል አንድ - መግቢያ - በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ስርአት/ፖሊሲ መዘርጋት - ለምን አስፈለገ?

- መንግስት ዓለምአቀፋዊ/አህጉራዊ ስምምነቶች/በህገ-መንግስቱ የተጣሉበትን የዜጎችን ሰብዓዊ/ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማክበር/ለማስከበር የተወሰዱ እርምጃዎች፣
- በተለይ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ለአለመግባባት፤ ግጭት፣ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መፍትሔ ይሰጣሉ፣ የመብት አያያዝ ያሻሽላሉ፣ የተባሉ ዘርፈ ብዙ የህግ/ተቋማዊ ማሻሻያዎች፣
- ሆኖም ባለፉት አመታት <u>በበርካታ የአገሪቱ አካባቢዎች አለመግባባቶች፣ ቅራኔዎች፣ ከባድ ግጭቶች እና ስር የሰደዱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች</u> ተባብሰዋል፡ የዚህ ውጤት -
    - በርካታ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው መፈናቀል፡ ለንብረት ውድመት፣ ለአካል ጉዳት እና ለሞት መዳረግ፤
    - በብዙ የአገሪቱ ክፍሎች ለዘመናት የዳበሩ የአብሮነት/የመቻቻል እሴቶች መላላት፣
    - በጥቅሉ በየጊዜው የሚነሱ አለመግባባቶች፣ ግጭቶች እና ከባድ የመብት ጥሰቶች <u>በሀገረ–መንግስቱ የዘላቂ ሰላም ግንባታ፣ የመብት አጠባበቅ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ፡</u>
- በቀደሙ አመታት - የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ ግጭቶች፣ ያልጠሩ ትርክቶች/በደሎችን ለመፍታት <u>ውስን ሙከራዎች ተደርገዋል፡</u>
    - ሆኖም ሙከራዎቹ በእውነት፣ በእርቅ፣ በምህረት እና በፍትህ ላይ የተዋቀሩ አልነበሩም፡
    - ተጎጂዎችን በማእከልነት አላሳተፉም፡
    - በግልፅ ፖሊሲ የሚመራ <u>ሁለተናዊ የሽግግር ፍትህ ስልትን አካታች፣ ሰብዓዊ መብት–ተኮር በሆነ እና በተሰናሰለ መንገድ አልተገበሩም፡</u>
    - በመሆኑም <u>ዘላቂ ለውጥ እና የተሟላ የተጠያቂነት ስርአትን</u> ማምጣት አልተቻለም፡

## መግቢያ - በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ስርአት/ፖሊሲ መዘርጋት - ለምን አስፈለገ?

- ስለሆነም ለአገራዊ ፈተናዎች ስር ነቀል እልባት ከመስጠት አንፃር –
  - ከነበሩ አገራዊ ሙከራዎች፣
  - የሌሎች አገራት መልካም ተሞክሮዎች፣
  - እንዲሁም አግባብነት ያላቸው የአለምአቀፍ ሰነዶች ስለ ሽግግር ፍትህ አካሄድ ያስቀመጧቸውን ደረጃዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣
    - ግጭቶች/የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በዘላቂነት ለማስቆም፣
    - ተጠያቂነት በማስፈን የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፣
      - የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር/ፖሊሲ ማውጣት አስፈላጊ ነው፡፡
- ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት/ሁሉን-አቀፍ ፍትህ ለማስፈን - አገሪቱ በተሟላ የሽግግር ፍትሕ ሂደት እንድታልፍ ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ተጨማሪ ማረጋገጫ፡
  - በፍትህ ሚኒስቴር ገለልተኛ የባለሙያዎች ቡድን የተደረገ ጥናት፣
  - የኢሰመኮ/የተመድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት ጣምራ የምርመራ ውጤት ምክረ-ሀሳብ፣
  - በፌዴራል መንግስት እና በህወሀት መካከል በደቡብ አፍሪካ በተፈረመው የሰላም ስምምነት፣

# መግቢያ - በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ስርአት/ፖሊሲ መዘርጋት - ለምን አስፈለገ?

- በመሆኑም ከነዚህ እውነቶች በመነሳት፡
  - በአገር አቀፍ ደረጃ በተደረጉ ሕዝባዊ ምክክሮች የተገኙ ግብዓቶችን፡
  - የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ያቀረባቸውን ምክረ-ሀሳቦች ታሳቢ በማድረግ፡
  - ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት እንዲቻል
    - አሳታፊ፣ አካታች፣ ከዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችና ጋር የተጣጣመ፣
    - መሰረታዊ የሽግግር ፍትሕ መርሆዎችን የተከተለ፣
    - የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ <u>የሽ/ፍትሕ ሂደት ፖሊሲ</u> ወጥቷል።

# መግቢያ - የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ዋና ዋና አምዶች

1 **የወንጀል ተጠያቂነት**

- ምርመራና ክስ የሚከናወንባቸው ወንጀሎች፣
- ምርመራና ክስ የሚከናወንባቸው አጥፊዎች፣
- የወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት፣
- የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት፣

2 **እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት፣ የዕርቅ ተግባር**

- እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት፣ ዕርቅ ስራ ተግባራዊ የሚደረግባቸው ጉዳዮች
- ተግባራቱ የሚከናወኑበት ተቋማዊ ሥርዓት

3 **በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት**

- ለምህረት ብቁ የማያደርጉ ሁኔታዎች
- ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች
- ምህረት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

4 **ማካካሻ**

- ተግባራዊ የሚደረጉ የማካካሻ ዓይነቶች/ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች
- ማካካሻ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት

5 **ተቋማዊ ማሻሻያ**

- የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ትኩረት የሚያደርግባቸው ተቋማት
- የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት

6 **የሽግግር ፍትህ ተግባራዊ የሚደረግበት የጊዜ ወሰን**

Made with Gamma

# መግቢያ - የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ዋና ዋና አምዶች

7 **በሽግግር ፍትህ ትግበራ የክልሎች ሚና**

8 **በሽግግር ፍትህ የባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች ሚና**

9 **የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች (cross-cutting issues)**

10 **የመንግስትና ባለድርሻ አካላት ሚና እና ክትትል/ድጋፍ ስርአት**

Made with Gamma

# ፖሊሲው የሚመራባቸው መርሆዎች

- ሰብአዊ መብት ተኮር ትግበራ፡- የሽግግር ፍትህን በሚመለከቱ ሰነዶች (አለም–አቀፍ/ብሄራዊ) ላይ የተቀመጡ ህጎችን፣ መርሆዎችንና ታሳቢ ያደረገ ይሆናል።
- ማንንም አለመጉዳት፡- የማንኛውንም ተሳታፊ/ተጎጂ ደህንነት በጠበቀ/ከዳግም ጥቃት/የጉዳት አደጋ የመጠበቅ መብትን በሚያረጋግጥ አግባብ ተግባራዊ ማድረግ፡
- ሀገራዊ ባለቤትነት፡- ሂደቱ ሃገራዊ ባለቤትነትን ባረጋገጠ አግባብ በመንግስት፣ በሕዝብ እና ቀጥተኛ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት፣ ባለቤትነት እና ውሳኔ ይመራል፡
- አውድ-ተኮር አተገባበር፡- አገራዊ እና አካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ፡ የሁሉንም ማ/ብ ክፍሎች ጥያቄ፡ የጋራ ትልም ያማከለ አካሄድ፡
- ተጠያቂነት፡- ሂደት ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ይመራል፡
- ሁለንተናዊነት፡- ሂደቱ የተለያዩ አላባዎችን በማቀናጀት በተናበበና ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ እንደአስፈላጊነቱም ቅደም ተከተልን በጠበቀ አግባብ ይተገበራል፡
- አካታችነትና አሳታፊነት፡- ሂደቱ በፖለቲካ አመለካከት፣ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ ወይም በሌላ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ልዩነትን ሳያስተናግድ፣ ሁሉን–አቀፍ፣ አካታች፣ በሀገሪቱ ያለውን ብዝሀነት በሚያንፀባርቅ እና ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በሚያሳትፍ መንገድ ይተገበራል።
- ስርአተ-ጾታ ተኮር አተገባበር፡- ሂደቱ ከቅድመ ዝግጅት ክዋኔዎች እስከ ሙሉ አተገባበር ሁሉ የሴቶች ተመጣጣኝ ውክልና/ትርጉም ያለው ተሳትፎ አሰራር፡
- ልዩ ትኩረት የሚሹ የህ/ብ ክፍሎች ተሳትፎ፡- ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎች ልዩ ፍላጎት/ምልከታን ግምት ውስት ያስገባ/ባለቤትነት የሚያረጋገጥ፡
- ቅንጅትና ትብብር፡- የሽግግር ፍትህ በህዝብ፣ በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ አጋር ድርጅቶች/ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ይተገበራል፡
- ሃገር በቀል ግጭት አፈታት እሴቶችን ጥቅም ላይ ማዋል፡- እንደአስፈላጊነቱ ተገቢ ማሻሻያዎችን እንዲያካሂዱ በማድረግ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል።

# ፖሊሲውን የማውጣት ስልጣን እና የፖሊሲው ዓላማ

- የተፈፃሚነት ወሰን - ይህ ፖሊሲ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል
- ፖሊሲውን የማውጣት ስልጣን
  - በህገ-መንግ አንቀጽ 51(2) የፌዴራል መንግስት በአገር-አቀፍ ደረጃ የሚተገበሩ ፖሊሲዎችን ለማውጣት/አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የተሰጠ ስልጣን፡፡ (social, eco, devt)
- የፖሊሲው ዓላማ
  - አጠቃላይ አላማ
    - የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አውድ መሰረት ያደረገ፣
    - የተቀናጀ የሽግግር ፍትህ ሂደት የሚመራበት ስርአት በመዘርጋት ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ፣ የህግ የበላይነት፣ ፍትህ እና ዲሞክራሲ የሚረጋገጥበትን መደላድል መፍጠር፡፡
  - ዝርዝር አላማዎች
    - የሽግግር ፍትህ ማእቀፍ አምዶቹ የሚኖራቸውን አላማ፣ ግብ፣ መስተጋብር እና የሚመሩባቸውን መሰረታዊ መርሆዎች እና ተቋማዊ አደረጃጀት በግልጽ ማመላከት፤
    - ለአተገባበራቸው ተገቢ የህግ፣ የአሰራር እና የአደረጃጀት አቅጣጫዎችን ማመላከት፤
    - የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው የተለያዩ ስልቶች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን የጊዜ ወሰን መመስረት፤
    - በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች እና ክልሎች የሚኖራቸውን ሚና መዘርዘር፤
    - ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብ. ክፍሎች/የመብት ጥሰት ሰለባዎች በሽ/ፍ ትግበራ የሚኖራቸውን ሚና/ሊደረግላቸው የሚገባውን ትኩረት ማስቀመጥ፡፡

# ክፍል ሁለት - የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች

# 1. የወንጀል ተጠያቂነት

- በሽግግር ፍትሕ ማእቀፍ የወንጀል ተጠያቂነትን መመስረት፣
  - ሀገሪቱ ያለባትን ዓለምአቀፍ ግዴታ ለመወጣት፣
  - የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ፣
  - ሰላም እና መረጋጋት ለማምጣት፣
  - የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና ተመሳሳይ ወንጀሎች እንዳይደገሙ ለማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

- በሽግግር ፍትሕ ሂደት፣
  - ምርመራ/ክስ የሚከናወንባቸው ወንጀሎች እና አጥፊዎች መለየት፣
  - የወንጀል ምርመራ፣ የክስ እና የፍርድ ሂደቶችን የሚያከናውኑ አካላትን ማንነት በፖሊሲው ማዕቀፍ በግልጽ ማመላከት ተገቢ ይሆናል።

# 1.1. ምርመራ እና ክስ የሚከናወንባቸው ጥሰቶች/ወንጀሎች

- ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፍ ሰነዶች፣ የአፍሪካ ህብረት የሽ/ፍ/ፖ፣ ሕገ-መንግስት -
  - በጉልህ የመብት ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎች ላይ የወንጀል ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጡ ያስገድዳሉ፡
  - በይቅርታም ሆነ በምህረት ሊታለፉ እንደማይገባ አስቀምጠዋል፡
- የሽግግር ፍትሕ ዋና ዓላማ ግብ የወንጀል ተጠያቂነት ስልትን ብቻ በመጠቀም ሁሉን–አቀፍ ፍትሕ ማምጣት አይደለም፡
  - ሁሉንም የሽግግር ስልቶች በተቀናጀ መልኩ በመተግበር ፍትሕ ማስፈን፣ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡
- በመሆኑም በሽግግር ፍትህ - በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎች ላይ ብቻ ያተኮረ ምርመራና ክስ ተግባራዊ ይደረጋል፡ (sys, widespread, patterned)
  - በወንጀል ምርመራና ክስ ሂደቱ የማይካተቱ ጉልህ ያልሆኑ ወንጀሎች/ጥፋቶች በሌሎች የሽግግር ፍትሕ ስልቶች ይታያሉ፡
- በተጨማሪም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-
  - ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎችን ለመለየት የሚያስችል ግልፅ መለያ መስፈርት ይዘረጋል፤
  - በወንጀል ሕግ ያልተካተቱ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በተመለከተ ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ አዲስ ሕግ ይወጣል፤
  - የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራዎችን በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችሉ ሥርዓቶች ይዘረጋሉ፡

## 1.2 ምርመራ የሚከናወንባቸው እና ክስ የሚመሰረትባቸው አጥፊዎች

- ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በሁሉም አጥፊዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ እና ክስ መመስረት ተመራጭ አካሄድ አይሆንም፡ አይቻልም፡
- የምርመራ እና ክስ የመመስረት ስራው ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ብቻ ይሆናል፡ ምክንያቶች፡
    - ከአጥፊዎቹ ብዛት፣
    - የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ከሚተገበርበት ሰፊ የጊዜ ወሰን ስፋት፣
    - በዓለም-አቀፍ ደረጃ ካለው የሽግግር ፍትሕ ተሞክሮ አኳያ፣
    - እንዲሁም የወንጀል ምርመራ/ክስ ለማካሄድ የሚያስፈልገው ረጅም ጊዜ/የሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪ፡
- በጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰት/ከባድ ወንጀል ድርጊት የተሳተፉ ነገር ግን ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ የሌላቸው አጥፊዎችን በተመለከተ፡
    - እንደየአግባብነቱ ሌሎች የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን በመጠቀም ጉዳያቸው የሚታይበት ሥርዓት ይዘረጋል፡
- አጥፊዎችን በተመለከተ የሚቀጥሉት ተጨማሪ የፖሊሲ አቅጣጫዎች/ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-
    - ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች የሚለዩበት ግልጽ ሥርዓት ይዘረጋል፤
    - በአጥፊዎች ላይ የወንጀል ሙሉ ተጠያቂነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ያለመከሰስ መብት ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ይደረጋል፤
    - በፖሊሲው/በማስፈፀሚያ ሕጎች፣ በሕገ-መንግስቱ፣ በወንጀል/በወንጀል ሥ/ሥ ሕጉ ላይ የተቀመጡ የምርመራ/ክስ መርሆዎች መሰረት ያደረገ ሂደት ይተገበራል፤

## 1.2 ምርመራ የሚከናወንባቸው እና ክስ የሚመሰረትባቸው አጥፊዎች

- በሀገር ውስጥ የማይገኙ ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ተጠያቂነትን - ከሚገኙበት አገር ተላልፈው እንዲሰጡ ተገቢ ስራ ይሰራል፤
- በምርመራ የማይደረስበት ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያለው አጥፊ የሚገኝበትን ቦታ ለጠቆመ ወይም አጥፊው በጉልሕ የሰብአዊ መብት ጥሰት/ከባድ ወንጀል መሳተፉን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ላቀረበ፥
    - የማበረታቻ ድጋፍ/ሽልማት ሥርዓት፤
- ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ምስክርነት ለሚሰጡ ሰዎች፥
    - የበቀል እርምጃ እንዳይደርስባቸው አስፈላጊ ጥበቃ እና ድጋፍ የሚያገኙበት ስርአት፡፡

## 1.3 የወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

- የምርመራ/የክስ ሂደቱ <u>ህዝባዊ አመኔታ እንዲያገኝ</u> እና የሽ/ፍ ስርአቱ በሀገር/በአለም-አቀፍ ደረጃ ቅቡል እንዲሆን ማድረግ ለሽ/ፍ/ ስኬት ጠቃሚ ነው፡፡
- በመሆኑም፣
  - የወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንባቸው ወንጀሎችን ግዝፈት እና ውስብስብነት፣
  - ሂደቱን ለመተግበር የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ወጪ/ሙያዊ አቅም፣
  - ሀገራችን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ

የወንጀል ምርመራ/ክስ <u>ስራዎችን የሚመራ ተቋማዊ ሥርዓት መመስረት</u> ያስፈልጋል፡

- ስለሆነም አሁን ካለው <u>የምርመራ/ዐቃቤ ሕግ ተቋም ውጪ በሆነ፣ ነጻ/ገለልተኛ ሆኖ ራሱን ችሎ በሚቋቋም፡</u> የሕዝብ አመኔታ በሚኖረው <u>አዲስ የልዩ ዐቃቤ ሕግ</u> ተቋም፡

# 1.3 የወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

**የወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ - ተጨማሪ የፖሊሲ አቅጣጫዎች እና ስልቶች፡-**

- የምርመራ ባለሙያዎች/ዐቃብያነ ህግ ምልመላ/ሹመት በስነ-ምግባር፣ ልምድ፣ ሙያዊ ብቃት፣ በህግ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ይከናወናል፣
- የባለሙያዎች ጥቆማ፣ ምልመላ እና ሹመት ያታን፣ አመኔታን፣ ገለልተኝነትን እና ብዝሃነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ይከናወናል፤
- የባለሙያዎች ጥቆማ፣ ዕጩዎችን የመመልመል/የመምረጥ፣ ለህ/ተ/ም/ቤት ለሹመት የማቅረብ ስራን የሚያከናውን ጊዜያዊ ኮሚቴ በህ/ተ/ም/ቤት ይቋቋማል፤
    - የኮሚቴው አባላት ከሕ/ተ/ም/ቤት፣ ከፍትህ ሚ/ር፣ ከኢሰመኮ፣ ከህግ ት/ቤቶች ኮንሶ፣ ጠበቆች ማህበር፣ ከፌ/ፖ/ኮሚሽን፣ ሲቪል ማ/ብ፤
- ለሚሰየሙ ባለሙያዎች አስፈላጊ ህጋዊ ጥበቃ እና ከለላ የሚደረግበት ሥርዓት ይዘረጋል፤
- የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ ነጻነቱን/ገለልተኝነቱን በሚያረጋግጥ አግባብ በቂ በጀት ይመደብለታል፤ የማስተዳደር ነጻነት እንዲኖረው ይደረጋል፤
- የተቋሙ ባለሙያዎች ከኃላፊነት የሚነሱበት/የሚተኩበት ስርዓት የተቋሙን ነጻነት/ገለልተኝነት በሚያረጋግጥ አግባብ እንዲዘረጋ ይደረጋል፤
- የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ ከሲቪል ሰርቪስ ውጭ ባለሙያዎች/ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የሚቀጥርበት/የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ይመሰረታል።

# 1.4 የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

- በሽ/ፍ ሂደት የወንጀል ተጠያቂነት ስራ የታለመውን ግብ እንዲያሳካ ለማስቻል ነጻ እና ገለልተኛ የዳኝነት ተቋም ማደራጀት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡
- ስለሆነም በሚተገበረው የሽ/ፍ ስርአት፣
  - የወንጀል ተጠያቂነት በመመስረት ሂደት ሀገራዊ ፍርድ ቤቶች ያላቸውን ቅድሚያ የመዳኘት ስልጣን በሚያከብር/በያጠናክር አግባብ፣
  - በማህበረሰቡ፣ በተጎጂዎች እና በተከሳሾች አመኔታ እና ቅቡልነት የሚኖረው፣
  - አቅም/ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን የሚያካትት፣
  - ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች የተለየ የራሱ አደረጃጀት የሚኖረው ነጻ እና ገለልተኛ ልዩ ፍርድ ቤት በህግ የሚቋቋም ይሆናል፡፡

## 1.4 የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

- የፍርድ ሂደትን በተመለከተ የሚከተሉት ተጨማሪ የፖሊሲ አቅጣጫዎች እና ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-
  - የልዩ ፍ/ቤቱን ነፃነት፣ ገለልተኛነት፣ ተአማኒነት ለማሳደግ፣ ሀገር-አቀፋዊ/ዓለም-አቀፋዊ ቅቡልነቱን ለማጠናከር የሚረዱ አደረጃጀቶች ይተገበራሉ፤
  - የሚሾሙ ዳኞች በሙብት ጥሰቶች ያልተሳተፉ/በሙብት ጥሰት የማይጠረጠሩ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የልየታ/ማጥራት ስራ ሥርዓት ይዘረጋል፤
  - የሚሾሙ ዳኞች በወንጀል ህግ፣ በአለምአቀፍ የወንጀል ህግ፣ በአለም-አቀፍ የሰብዓዊነት ህግጋት፣ በአለም-አቀፍ የሰብዓዊ ሙብቶች እና በአለም-አቀፍ የጦር ህግ ጉዳዮች ከፍተኛ ልምድ፣ የላቀ ብቃት እና እውቀት ያላቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፤
  - የዳኞች ምልመላ/ሹመት በስነ-ምግባር፣ ልምድ እና ሙያዊ ብቃት በህግ በሚቀመጡ ሌሎች መስፈርቶች መሰረት ይካሄዳል፤
  - የዳኞች ጥቆማ፣ ምልመላ፣ ሹመት ፆታን፣ አመኔታን፣ ገለልተኝነትን፣ ብዝሃነትን በሚያረጋግጥ አግባብ አሳታፊና ግልጽ በሆነ ሂደት ይከናወናል፤
  - የዳኞች ጥቆማን የመቀበል እና የምልመላ/የመረጣ ስራው በህ/ተ/ም/ቤት በሚቋቋም ነጻ እና ገለልተኛ ጊዜያዊ ኮሚቴ ይከናወናል፤
  - የኮሚቴው አባላት ከፍርድ ቤት፣ ከህ/ተ/ም/ቤት፣ ኢሰመኮ፣ ህግ ት/ቤቶች ኮንሶርቲየም፣ ሲቪል ማህ/ብ ተቋማት፣ ከጠበቆች ማህበር ይውጣጣል፣
  - ለዳኝነት የተጠቆሙ/የተለዩ እጩዎች ለህዝብ ይፋ የሚደረጉበት/ህዝብ አስተያየት የሚያቀርብበት ስርዓት ይዘረጋል፤
  - በዚህ ሂደት የሚለዩ ዕጩ ዳኞች ለህ/ተ/ም/ቤት ቀርበው የሚሾሙበት ዝርዝር አሰራር በህግ ይወሰናል፤

## 1.4 የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

- ልዩ ፍርድ ቤቱ በስሩ የሚያርፉ የስረ-ነገር ጉዳዮችን በተመለከተ ቅድሚያ የዳኝነት ስልጣን እንዲኖረው ይደረጋል፤
- ልዩ ፍርድ ቤቱ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የስረ-ነገር ስልጣን የሚኖራቸው የመጀመሪያ ደረጃ እና የይግባኝ ምድቦች እንዲኖሩት ይደረጋል፤
- ሙያዊ ብቃት/ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን ያካተተ የሬጅስትራር እና የተከላካይ ጠበቃ አደረጃጀት፣ የተጎጂዎች ማስተባበሪያ፣ የአማካሪ ባለሙያዎች እና ሌሎች ደጋፊ የስራ ሂደቶች፤
- ልዩ ፍርድ ቤቱ የዳኝነት ስራውን የሀገር ውስጥ ህጎችን እና እንዳስፈላጊነቱ ዓለም-አቀፍ ህግ እና መርህን በመከተል የሚሰራ ይሆናል፡
- ዳኞች የሚነሱበት/የሚተኩበት ሂደት የልዩ ፍ/ቤቱን ነጻነት እና ገለልተኝነት በሚያረጋግጥ አግባብ እንዲሆን የህግ እና የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ልዩ ፍርድ ቤቱ ከሲቪል ሰርቪስ አሰራር በተለየ ሁኔታ የራሱን የባለሙያ/ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የሚቀጥርበት/የሚያስተዳድርበት ሥርዓት፤
- ተቋማዊ ነጻነት/ገለልተኝነት በሚያረጋግጥ አግባብ በቂ በጀት ይመደባል፤ የበጀት አስተዳደር ነጻነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ይዘረጋል።

# 2. እውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የእርቅ ተግባራት

- እውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የእርቅ ተግባራት፡
    - በዘመናት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መሰረታዊ ምክንያት በመለየት የተጎጂዎችን እውነቱን የማወቅ መብት ለማረጋገጥ ያስችላሉ፡
    - ተለያይተው የነበሩ ሰዎች/የሕብ/ ክፍሎች ግንኙነታቸውን ለመገንባት፣ ቁስላቸውን ለመፈወስ፣ በደሎች እንዳይደገሙ ለማድረግ ፋይዳ አላቸው፡
- ስለሆነም እውነት የማፈላለግ፣ ማውጣት እና የእርቅ ተግባር - ከሌሎች የሽግግር ፍትህ ዓላባዎች ጋር በተናበበ መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል፡
- እውነት የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የእርቅ ስራ፥
    - 'በሁሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' ላይ ያተኩራል፡ (በወንጀል ተጠያቂነት ከሚሸፈኑ ጉልህ - ከፍተኛ ተጠያቂ ውጭ ያሉትን)
        - የጥሰቶችን መሠረታዊ ምክንያቶች፣ ተከታታይነት፣ ስልታዊነት፣ መጠነ-ሰፊነት፣ መጠን ይለያል፡
    - ሌሎች 'ጉልህ ያልሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' - በባህላዊ/ክልል–አቀፍ የግጭት አፈታት/እርቅ ሥርዓቶች የሥረ-ነገር ስልጣን ስር ያርፋሉ፡

## 2.1. እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና ዕርቅ ተግባራዊ የሚደረግባቸው ጉዳዮች

- የሂደቱ ስረ-ነገር 'በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች' ላይ የሚወድቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፥
  - ሂደቱ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ጥሰቶች ግን በመብት ጥሰቶቹ ክብደት/ጉልህነት ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚወሰን አይሆንም፤
  - የድርጊቶቹን ተከታታይነት፣ ስልታዊነት ወይም መጠነ-ሰፊነት ግምት ውስጥ በማስገባት መሰል ጥሰቶች የሂደቱ አካል ይደረጋሉ፤
- በተለያዩ ጊዜያት ለግጭት መንስኤ የሆኑ የታሪክ አረዳዶች/ትርክቶች – የተከሰቱበት የጊዜ ማእቀፍ ወሰን ሳይደረግበት ሁሉም እንዲሸፈኑ ይሆናል፡
- በሀቅ ኮሚሽን ፊት በፈቃዳቸው በመቅረብ እውነትን የሚያወጡ/ቃል የሚሰጡ አጥፊዎች የሰጡት ማናቸውም ቃል በፍርድ ሂደት እንደ ማስረጃ ጥቅም ላይ እንዳይውል ጥበቃ (use immunity) ይደረጋል፤
- ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ጉዳታቸውን በዝርዝር እንዲያስረዱ በማድረግ እውነትን በማጥራት ሂደት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል፤
- ሂደቶቹ ለጾታዊ ጥሰቶች፣ ለተፈናቃዮች ልዩ በደሎች እና ለሌሎች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ጉዳቶች ተገቢ ትኩረት በሚሰጥ አግባብ ይከናወናሉ፤
- የከፍተኛ መብት ጥሰቶችን ዝርዝር መረጃዎች በአግባቡ የመሰነድ፤ ለማ/ብ የማሳወቅ፤ ለተጎጂዎች ሕዝባዊ እውቅና የመስጠት አሰራሮች ይዘረጋሉ።

## 2.2. እውነትን የማፈላለግ፡ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባር የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

- የእውነት ማፈላለግ/የእርቅ ስራ – ነጻነትን፣ ገለልተኛነት፣ ቅቡልነት በሚያረጋግጥ/ብቃት በተላበሰ መንገድ የሚተገበርበት ተቋማዊ ሥርዓት አስፈላጊ ነው፡፡
    - ስለሆነም ተግባራቱ ከፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ/ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም አዲስ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት እንዲከናወኑ ይደረጋል፡
- ተግባራቱ የሚከናወኑበት ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ የሚከተሉት አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-
    - ኮሚሽኑ ምህረት የመስጠት ሥራን የሚመለከት ተደራቢ ኃላፊነት ይኖረዋል፤
    - የማካካሻ ስራዎችን የሚመራ መዋቅር በሥሩ ያደራጃል፤
    - ኮሚሽኑ የጾታ፣ ሀገር ሽማግሌዎች፣ ሀይማኖት አባቶች፣ የሲቪክ ማ/ብ፣ ሌሎች የማ/ብ ክፍሎች ውክልና ያለው ሆኖ ብቁ/ገለልተኛ ባለሙያዎችን ያካትታል፡
    - ለኮሚሽነርነት የሚያበቁ ዝርዝር ጉዳዮች በሕግ ይደነገጋሉ፤ የኮሚሽነሮች ምርጫ የሕዝብ/ባለድርሻ አካላትን አስተያየት ግምት ውስጥ ያስገባል፡
    - የኮሚሽነሮች መረጣ እና ሹመት የፆታ፣ እውቀት፣ ግብረገብነት፣ ሙያዊ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት እና የብዝሃነት መገለጫዎችን ታሳቢ ያደርጋል፡
    - የኮሚሽነሮችን ጥቆማ የመቀበል፣ የምልመላ እና የመረጣ ስራ በህ/ተ/ም/ቤት በሚሰየም ገለልተኛ ጊዜያዊ ኮሚቴ ይካሄዳል፤
        - የኮሚቴው አባላት ከሲቪክ ማ/ብ አደረጃጀት፣ ከዩኒቨርሲቲ እና ከታዋቂ ሰዎች መካከል የሚውጣጡ ይሆናል፤
        - ኮሚቴው የመረጣ ስራውን ሲያጠናቅቅ ለህ/ተ/ም/ቤት ያቀርባል፤

## 2.2 እውነትን የማፈላለግ፡ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባር የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

- የኮሚሽኑን ተቋማዊ ብቃት ለማጎልበት/ልምድ ለመቅሰም፣ ከተዓማኒነት ጋር የሚያያዙ ጥያቄዎችን ለመመለስ
    - ልምድ ያላቸው የውጭ ባለሙያዎች በኮሚሽኑ አደረጃጀት ውስጥ በአማካሪነት እና ድጋፍ ሰጪነት እንዲካተቱ ይደረጋል፤
- በትግበራ ምእራፍ የኮሚሽኑን ነጻነት/ገለልተኝነት የሚያረጋግጡ አሠራሮች ይዘረጋሉ፤
    - ከሲቪል ሰርቪስ መዋቅር በተለየ መንገድ ባለሙያዎች/ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የሚቀጥርበት እና የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ይዘረጋል፤
    - በቂ በጀት/በጀቱን የሚያስተዳድርበት ነጻነት ይኖረዋል።

# 3. በቅድመ–ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት

- የሽግግር ፍትህ ሂደቱ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ጥሰቶችን ይዳስሳል፣
  - ስለሆነም የተጎጂዎች/የአጥፊዎች ቁጥር እጅግ ከፍተኛ እንደሚሆን ይጠበቃል፣
  - በዚህ ረገድ ሁሉንም ወንጀሎች/ጥሰቶች በክስ ሂደት እንዲያልፉ ማድረግ አይቻልም፣
  - በሌላ በኩል ለተፈጸሙ ጥሰቶች ሁሉ ምህረት የሚሰጥበትን ሁኔታ መደንገግ፣
    - የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስቀር፣ ዓለምአቀፍ ግዴታን የሚቃረን ነው፣
    - የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ ለማድረግ ተግዳሮት ይፈጥራል፣
    - ስለሆነም በቅድመ–ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረትን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።
    - በኢትዮጵያ ተግባራዊ የሚደረገው የሽግግር ፍትሕ ሂደት በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ምህረት አሰራርን ተፈፃሚ ያደርጋል።

# 3.1. ለምህረት ብቁ የማያደርጉ እና የሚያደርጉ ሁኔታዎች

## ለምህረት ብቁ የማያደርጉ ሁኔታዎች

- ዓለምአቀፍ ሰነዶችና የሰብዐዊነት ሕጎች ጉልህ የሰብዐዊ መብት ጥሰቶችን የፈፀሙ አጥፊዎች ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይኖርባቸው ደንግገዋል፡
- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስትም በአንቀጽ 28(1) ላይ በምህረት ሊታለፉ የማይችሉ ወንጀሎችን ዘርዝሮ አስቀምጧል፡
- በመሆኑም በፖሊሲው 'ለወንጀል ተጠያቂነት' ዓላማ 'ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች' እና 'ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎችን' በተመለከተ በተሰጠው ትርጉም መሰረት -
    - 'በጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች' በማናቸውም መልኩ የሚሰጥ ምህረት ተጠቃሚ አይሆኑም።

## 3.1. ለምህረት ብቁ የማያደርጉ እና የሚያደርጉ ሁኔታዎች

### ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

- በቅድመ–ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ምህረት የሽግግር ፍትሕ ሂደትን በማሳለጥ ረገድ የጎላ ሚና ይኖረዋል፡
- ምህረት ዓላማውን እንዲያሳካ እና ተጠቃሚው ወደ ህብ/ ሲቀላቀል በቀል እንዳይፈጠር ለመከላከል ሂደቱ ተጎጂን ማዕከል እንዲያደርግ እና በፖሊሲው የተገለጹ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ሚና ከግምት እንዲያስገባ ይደረጋል፤
- እንደሁኔታው ማመልከቻ በማቅረብ የምህረት ተጠቃሚ ለመሆን የሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይደረጋሉ፦
    - በጉልህ ወንጀሎች/ጥሰቶች ላይ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያለው አለመሆን፤
    - እውነት በማውጣት እና በምርመራ ሂደት መተባበር፤
    - ጥፋትን ማመን እና መጸጸት፤ በይፋ ህዝብን/ተጎጂዎችን ይቅርታ መጠየቅ፤ እንደ ሁኔታው ለበደል በማካካሻ ሂደት ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆን፤
    - በበጎ ፈቃድ ስራ ላይ በመሳተፍ ህዝባዊ አገልግሎት ለመስጠት መስማማት፤
    - ወንጀሉ የተፈፀመበትን ምክንያት (motive) በማየት እንዳስፈላጊነቱ ከህዝባዊ ሀላፊነት ወይም ስልጣን ለመልቀቅ ፈቃደኛ መሆን፤
    - ተመሳሳይ የወንጀል ሪከርድ አለመኖር፤ ተመሳሳይ ጥሰቶች እንደማይፈጸም ቃል መግባት፤
- የምህረት አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽ፣ ገለልተኛ እና ተአማኒነት በሚኖረው አግባብ ይከናወናል፤ ዝርዝሩ በህግ እንዲወሰን ይደረጋል።

# 3.2. የምህረት ተግባር የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት

- ምህረትን - ከእውነት ማፈላለግ፣ ማውጣትና ከእርቅ ተግባራት ጋር በተሰናሰለ እና ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ መተግበር አስፈላጊ ነው፡
- ይህን ለማድረግ እንዲቻል የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑ – ምህረት የመስጠቱን ተግባር በተደራቢነት እንዲያከናውን ይደረጋል፡

**የምህረት አሰጣጥ ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስልቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-**

- ገለልተኛ የሆነ፣ በዘርፉ የዳበረ እውቀት እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በአማካሪነት የያዘ መዋቅር በኮሚሽኑ ስር ይደራጃል፤
- የሚዋቀረው አደረጃጀት የምህረት ጥያቄን ከመቀበል አንስቶ በአቤቱታዎች ላይ ለኮሚሽኑ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብበት ስርዐት በህግ ይዘረጋል፤

# 4. ማካካሻ

- በመብት ጥሰቶች/ኢፍትሀዊ አሰራሮች ተጎጂ የሆኑ ግለሰቦች/ማህበ የጉዳቶችን ዓይነት/መጠን በሚሸፍን የማካካሻ ስርዐት እንዲያልፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡
  - መልሶ ማቋቋም፣ ማገገሚያ፣ እርካታ፣ የመታሰቢያ/ማስታወሻ ክንዋኔ፣ በይፋ ይቅርታ መጠየቅ፡ ሌሎች ማካካሻዎች የሚተገብር ስርዐት ይደራጃል፡

## 4.1. ተግባራዊ የሚደረጉ የማካካሻ ዓይነቶች እና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች

- በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የሚከተሉት የማካካሻ አይነቶች አቅምን እና ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-
  - መልሶ ማቋቋም፣ ማገገሚያ፣ እርካታ፣ የመታሰቢያ/ማስታወሻ ክንዋኔዎች፣ የጥሰቶችን ሙሉ ሀቅ ማፈላለግ፡ ይፋ ማውጣት እና እውቅና መስጠት፤
  - ለተፈጸሙ በደሎች በመንግስት ደረጃ ይፋዊ ይቅርታ መጠየቅ፤
  - ዘላቂ የማካካሻ ስርአት ተግባራዊ እስኪደረግ ድረስ ጣልቃ-ገብ የማካካሻ እና ድጋፍ ተግባራት ይከናወናሉ፡-
    - መልሶ ማቋቋም፣ የማገገሚያ እርምጃዎች እና ሌሎች አስፈላጊ የማካካሻ ዓይነቶች፡
    - አላማው የተጎጂዎችን አንገብጋቢ/አስቸኳይ ችግሮችን፡ የሕጻናት፣ የሴቶች፣ የተፈናቃዮች፣ የአካል ጉዳተኞች፡ የአዛውንቶችን ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት በተወሰነ መልኩ መቅረፍ ይሆናል፡
- የማካካሻ አይነቶች ሲተገበሩ አይነታቸውን፣ ባህሪያቸውን፡ ሂደቶቹን መሰረት በማድረግ ባህላዊ የፍትሕ ተቋማት ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፤
- የማካካሻ አተገባበር የተጎጂ ህ/ብ ክፍሎችን (የሕጻናት፣ የሴቶች፣ የተፈናቃዮች፣ የአካል ጉዳተኞች፡ የአዛውንቶች) ፍላጎት ባገናዘበ መንገድ ይፈፀማል።

## 4.2. ማካካሻ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት

- የማካካሻ ስራን – ምህረት ከመስጠት፣ እና ከእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣትና እርቅ ተግባር ጋር በተሰናሰነ መንገድ መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡
  - ስለሆነም የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑ የማካካሻ ስራዎችን የሚያከናውን ይሆናል፡

በዚህ ረገድ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡-

- ማካካሻ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በጥናት ላይ የተመሰረተ የማካካሻ ህግ ማዕቀፍ/መርሀግብር ይዘጋጃል፡
- ተጎጂዎችን የማቋቋም/የመደገፍ ሥራዎችን ለመምራት የማቋቋሚያ እና ድጋፍ ፈንድ በህግ ይቋቋማል፤
- ገለልተኛ የሆነ፣ የኮሚሽኑን የማካካሻ ስራዎች የሚያሳልጥ እና የዘርፉ ባለሙያዎችን በአማካሪነት የያዘ መዋቅር በኮሚሽኑ ስር ይደራጃል፤
  - አደረጃጀቱ የማካካሻ ማዕቀፍ/መርሀግብር ይነድፋል፤ በአቤቱታዎች/ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ለኮሚሽኑ የውሳኔ ሀሳብ የሚቀርብበት ስርዐት ይዘረጋል፡፡

# 5. ተቋማዊ ማሻሻያ

- በከባድ ጥሰቶች በቀጥታም/በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ የነበራቸውን ተቋማት/ሰዎች/ኃላፊዎች ማስቀጠል ለሽግግር ሂደት እንቅፋት ይፈጥራል፡
- በእነዚህ ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ -
    - ጥሰቶቹ እንዳይደገሙ፣ ተቋማቱ የሕዝብ አመኔታ እንዲኖራቸው፣ መብቶችን የማክበር/ማስከበር ቁመና እንዲያገኙ ይረዳል፡
- ስለሆነም በሚተገበረው የሽግግር ፍትህ ሂደት ሰፊ የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ተግባራዊ ይደረጋል፡
- የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎችም ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-
    - ተቋማት፣ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች በተፈፀሙ ጥሰቶች/ወንጀሎች የነበራቸው ድርሻ፣ ለተፈፀሙ ጥሰቶች መነሻ የሆኑ ወይም አስቻይ ሁኔታዎችን የፈጠሩ የፖሊሲ፣ የህግ እና የአሰራር ማዕቀፎችን ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት መርሆዎችን/አሰራሮችን ባከበረ መልኩ ይለያሉ፤
    - በቀጥታ/በተዘዋዋሪ መንገድ በመሳተፍ ወይም ኃላፊነትን ባለመወጣት በተፈፀሙ ጥሰቶች ላይ እንደነበራቸው የተሳትፎ መጠን ወይም የሥነ-ምግባር/ሙያዊ ብቃት ማነስ ሁኔታ እየታየ፥
        - ከስራ እንዲነሱ፣ በአስተዳደራዊ እርምጃ/በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ወይም ሌሎች እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይደረጋል፤
    - የተለዩ/ለጥሰት መነሻ የሆኑ ምንጮችን መሰረት በማድረግ ተቋማትን ለማሻሻል የሚያስችሉ የአጭር/ረጅም ጊዜ ፕሮግራሞች ይተገበራሉ፡

# 6. ተቋማዊ ማሻሻያ

- ተቋማት፣ ኃላፊዎች/ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን ተቋማዊ/ሙያዊ ነጻነት እና ገለልተኝነት ባስጠበቀ አግባብ እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችል የተቋም ስልጣን፣ አደረጃጀት እና ተጠሪነትን የሚመለከቱ የህግ፣ የፖሊሲ ወይም አሰራር ማሻሻያዎች ይደረጋሉ፤
- የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች/ወንጀሎች እንዳይደገሙ እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለመልካም አስተዳደር አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥሩ የህግ/ፖሊሲ ማዕቀፎች ይወጣሉ፤
- ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የህ/ብ ክፍሎት ትኩረት የሚሰጥ እና ህብ/ን ማዕከል የሚያደርግ የተቋማት የወንጀል መከላከል አቅም ማጠናከሪያ ስልት በጥናት ላይ ተመስርቶ ይተገበራል፤
- ተቋማት መልካም ሥነ-ምግባር/ሙያዊ ብቃት ባላቸው ታማኝ፣ ነጻ እና ገለልተኛ የሥራ ኃላፊዎች እንዲመሩ ይደረጋል፤
- ተቋማት ሙያዊ ብቃት/መልካም ሥነ-ምግባር ባላቸው ታማኝ፣ ነጻ እና ገለልተኛ ባለሙያዎች እንዲደራጁ የሚያስችል የቅጥር/ምልመላ ሥርዓት ይዘረጋል፤
- አቅም በፈቀደ መጠን ለተቋማት የሚመደብ በጀት እና የሰው ኃይል ብዛት እና ጥራት በማሳደግ የሕዝብ አገልግሎት እንዲሻሻል ይደረጋል፤
- የተቋማት ኃላፊዎች እና ሰራተኞችን የሰብዓዊ መብት አያያዝ፣ አገልግሎት አሰጣጥ ቀጣይነት ያለው የስልጠና መርሀግብር በመስጠት አቅም የማሳደግ ስራ ይሰራል፤
- ዜጎች እና አገልግሎት ጠያቂዎች በተቋማት ላይ ቅሬታ የሚያቀርቡበት እና ምላሽ የሚያገኙበት ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
- የተፈፀሙ የመብት ጥሰቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ በፌዴራል ተቋማት/በፌዴራል እና በክልል ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል፡
- የልየታ፣ የማጥራት እና የማሻሻያ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ሁሉን አቀፍ ህግ እንዲወጣ ይደረጋል።

## 6.1. የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ትኩረት የሚያደርግባቸው ተቋማት

- ከመብቶች ጥበቃ/አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ሀላፊነት ያላቸው ሁሉም ተቋማት መብቶች/ነጻነቶችን የማክበር/የማስከበር ግዴታቸውን መወጣት እንዲችሉ ለማድረግ በትኩረት መስራት መሰረታዊ ሁኔታ ነው፡
- ሆኖም ካለው ውሰን አገራዊ አቅም እና የሽግግር ፍትህ ሂደት ባህሪ አንጻር ሁሉንም ተቋማት በማሻሻያ ሥርዓት ሂደት እንዲያልፉ ማድረግ አይቻልም፡
  - በሽግግር ፍትህ ሂደት ማእቀፍ የማሻሻያ ስራዎች ትግበራ ትኩረት ውሰን ይሆናል፡
  - በዋናነት በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ በተሳተፉ ሰዎች፣ መብቶች በማክበር/በማስከበር ረገድ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ፡ እና ያለፉ ጥፋቶች እንዳይደገሙ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ በሚችሉት ላይ ይሆናል፡ በዋናነትም፡-
    - አገራዊ/ክልላዊ የፍትህ፣ የፀጥታ እና የደህንነት ተቋማት፣
    - የሚዲያ ተቋማት፣
    - ልዩ ትኩረት የሚሹ የህ/ብ ክፍሎች ሰብዓዊ መብትን ከማስከበር አኳያ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ ተቋማት፣ እና
    - ለሰብዓዊ መብት ጥሰት አስቻይ ሁኔታን በፈጠሩ ህጎች፣ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ላይ ቅድሚያ በመስጠት የሚተገበር ይሆናል።

## 6.2 የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት

- የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ቅቡል፡ የህዝብ አመኔታ እንዲኖረው ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ባለው ተቋም እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል
  - ስለሆነም ስራውን የሚመራ ነጻ፣ ገለልተኛ እና የህዝብ አመኔታ ያለው ኮሚሽን በህግ እንዲቋቋም ይደረጋል።
- የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-
  - ኮሚሽኑ ሙያዊ ብቃት፣ ልምድ፣ መልካም ስነ-ምግባር ባላቸው ነጻ/ከፖለቲካ ገለልተኛ በሆኑ ኮሚሽነሮች/ባለሙያዎች ይመራል፡
  - ኮሚሽኑ ተቋማትን የመለየት/የማጥራት ስራ በማከናወን/ማሻሻያዎችን በመለየት ለህ/ተ/ም/ቤት አቅርቦ የማስወሰን ስልጣን እንዲኖረው ይደረጋል፤
  - በሚመረጡ ተቋማት ላይ የመለየት እና የማጥራት ሂደቱ የሚመራበት ዝርዝር ሥርዓት ይዘረጋል፤

  - ከዳኝነት አካላት ጋር በተገናኘ፥
    - ኮሚሽኑ የዳኞችን ልየታ እና ማጥራት ስራ የሚያከናውን ራሱን የቻለ አደረጃጀት ይኖረዋል፤
    - የዳኞች ልየታ/ማጥራት ስራው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ–መንግስት ከተቀመጡ ጥበቃዎች/አሰራሮች ጋር በሚጣጣም አግባብ በኮሚሽኑ ይከናወናል፤

## 6.2 የተቋማዊ ማሻሻያ ስራ የሚመራበት ተቋማዊ ሥርዓት

- ኮሚሽኑ የመለየት/ማጥራት ስራውን ሲያከናውን - በተቋማቱ የሚገኙ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል፤
- የሽግግር ፍትህ ተቋማዊ ማሻሻያ ዓላማዎችን በሚያሳካ አግባብ ለማከናወን እንዲቻል ልምድ/እውቀት ያላቸው አማካሪዎች እንዲኖሩት ይደረጋል፤
- የኮሚሽነሮች ጥቆማ፣ ምልመላ/መረጣ ስራዎችን የሚያከናውን ከሲቪክ ማህ/ብ፣ ከዩኒቨርሲቲ እና ከታዋቂ ግለሰቦች የሚውጣጣ ገለልተኛ ጊዜያዊ ኮሚቴ ይቋቋማል፤
  - ኮሚቴው ለፓርላማ ያቀርባል፤
- ተቋማዊ ነጻነት በሚያረጋግጥ መጠን በጀት ይኖረዋል፣ ከሲቪል ሰርቪስ መዋቅር በተለየ ራሱን የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

- ክልሎች የተቋማዊ ማሻሻያ የሚሰራ ተቋም በህግ ያቋቁማሉ፤
  - ተቋማቱ ከዚህ ፖሊሲ/የሰብዓዊ መብት መርሆዎች ጋር በሚጣጣም አግባብ የሚመሰረቱ ይሆናል፤
- ኮሚሽኑ በክልል የሚሰሩ የልየታ፣ የማጥራት እና የማሻሻያ ስራዎችን በቅርበት የመደገፍ እና የማስተባበር ሚና እንዲኖረው ይደረጋል።

# 7. የሽግግር ፍትህ ተግባራዊ የሚደረግበት የጊዜ ወሰን

- የሽግግር ፍትህ ስርአት ትግበራ ግልፅ የጊዜ ወሰን ሊኖረው ይገባል፡
- ለዚህ አላማ የሚቀመጥ የጊዜ ወሰን በተቻለ መጠን ሁሉ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን፣ የተዛነፉ የታሪክ አረዳዶች፣ ልዩነቶች እና ቁርሾዎች፣ እና የተከሰቱ በደሎችን የሚያካትት እና ለዘላቂ ሽግግር መንገድ የሚከፍት መሆን አለበት።
- ስለሆነም የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን፥
    - ለወንጀል ተጠያቂነት አላማ 'የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ–መንግስት ከፀደቀበት ከ1987 ጀምሮ' ያለው የጊዜ ወሰን ተፈፃሚ ይደረጋል፡
    - 'ለእውነት ማፈላለግ፣ እርቅ ማስፈን እና ማካካሻ ስራዎች አላማ' ወሰኑ 'መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ' ይሆናል፡
        - ይህም ጥሰቶች/ቅራኔዎችን ከመሰረታቸው በማጥራት ለመመርመር፣ ስብራቶች እንዲሽሩ/እንዲጠገኑ፣ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ይስችላል።

# 8. በሽግግር ፍትህ ትግበራ የክልሎች ሚና

- በሽ/ፍ ትግበራ ክልሎች የሚኖራቸውን ሚና ዘርዝሮ ማስቀመጥ መልካም የስራ ግንኙነት በመፍጠር የሽ/ፍትህ አላማዎችን ለማሳካት አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በፖሊሲ እየተመራ በሚተገበረው የሽግግር ፍትህ ስርአት - ክልሎች ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፡
- ክልሎች በሁለት መንገዶች የሚገለፁ ሚናዎች ይኖሯቸዋል።
    - የመጀመሪያው በአገር–አቀፍ ተቋማት የሚከናወኑ ስራዎችን በማገዝ ላይ የሚያተኩር ነው፣
    - ሁለተኛው በሀገራዊ ፖሊሲው አጠቃላይ እሳቤዎች/እሴቶች ላይ በመመስረት ውስን የሽ/ፍ ስራዎችን በባለቤትነት የሚመሩበትን ሂደት ነው።

በአገር–አቀፍ ተቋማት የሚከናወኑ ስራዎችን በማገዝ ረገድ ክልሎች የሚከተሉት ሀላፊነቶች ይኖሯቸዋል፦

- ለአገራዊ ሽግግር ፍትህ ሂደት አጋዥ የሆኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችን መለየት/ማሳወቅ፤
- ተጎጂዎችን መለየት፣ የማካካሻ ሂደቱን በገንዘብና ሌሎች መንገዶች ማገዝ፤ ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋም፣ የስራ እድሎችን መፍጠር፤
- ማስታወሻ/ሐውልት ማቆም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቦታ መለየት፣ ማቅረብ እና በሂደቱ መሳተፍ፤
- ለሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚጠቅም መረጃና ማስረጃ ማሰባሰብ፣ አደራጅቶ ማቅረብ፤

# 8. በሽግግር ፍትህ ትግበራ የክልሎች ሚና

- በወንጀል የተሳተፈ ሰውን አሳልፎ መስጠት፤ ጥፋተኞችን ሪፖርት ማድረግ እና ለፍርድ ማቅረብ፣ ፍትህን ለማረጋገጥ በቅንጅት መሥራት፤
- የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ለማስፈጸም ለሚሳተፉ አካላት ምቹ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፣ ደህንነታቸውን መጠበቅ፤
- የሚያስተዳድሩት ህዝብ በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ላይ አመኔታ እንዲኖረው መስራት፤
- የህዝቦች አብሮነት እና ግንኙነት የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት፣ ሀሳብ ማመንጨት እና የየክልሉ ህዝብ ተሳታፊነትን ማረጋገጥ።

‘በአገራዊ የሽ/ፍትሕ የማይሸፈኑ ጉዳዮች፣ ጥሰቶች እና ግጭቶችን’ በተመለከተ ክልሎች የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በባለቤትነት ይተገብራሉ።

- ‘በአገራዊ የሽግግር ፍትሕ ሂደት የማይሸፈኑ’ የእርቅ እና የማካካሻ ስርዐቶችን ከአገራዊ መርሆችና መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር፤
- በተመሳሳይ መርሆች ላይ ተመስርተው የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና እውቅና የመስጠት ስራዎችን ማከናወን፤
- ለተፈጸሙ በደሎች በመንግስት ደረጃ ይቅርታ መጠየቅ፤
- ለተጎጂዎች የመልሶ ማቋቋም፣ የማገገሚያ፣ የመታሰቢያ እና ማስታወሻ ስርዐቶችን መቅረፅ እና መተግበር፤
- በአገር-አቀፍ ደረጃ በሚወጡ መስፈርቶች መሰረት በህጎቻቸው/ተቋሞቻቸው ላይ ማሻሻያዎችን ማከናወን፤
- በሽ/ፍ ሂደቱ የሚሳተፉ የባህል ፍትህ ሥርአቶችን ከመርሆች/መስፈርቶች አንፃር መለየት እውቅና መስጠት፣ አሰራራቸውን በህግ መደንገግ።

# 9. በሽግግር ፍትህ የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቶች ሚና

- በአገራችን ለዘመናት ሲተገበሩ የቆዩ በርካታ ባህላዊ/ሀይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አሉ፡
  - በማህ/ብ ሆነ በግለሰብ ደረጃ ለሚከሰቱ ግጭቶችን በእውነት/በይቅርታ ላይ የተመሰረተ ፍትህ ይሰጣሉ፣ ስብራቶችን ይጠግናሉ፡ ሰላም ያሰፍናሉ፡
  - በሽ/ፍትህ ሂደቱ የሚጫወቱትን አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ሚና ለይቶ ጥቅም ላይ ማዋል የሽ/ፍትህን አላማ ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡
- ስለሆነም ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ክፍተቶቻቸውን በመሙላት፡
  - በሽ/ፍ ሂደት ከሌሎች የሽ/ፍ ተቋማት ጋር በመቀናጀት እውነትን በማፈላለግ፣ እርቅ በማስፈን፣ በማካካሻ እና በምህረት መስጠት ተግባራት፣
  - ማህበረሰባዊ ሰላምን ለማስፈን በሚደረጉ ስራዎች ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፡

# 9. በሽግግር ፍትህ የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቶች ሚና

**ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በተመለከተ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡**

- እውነትን በማፈላለግ፣ ተጠያቂዎች ለፍትህ እንዲቀርቡ በመርዳት፣ በእርቅ እና በማካካሻ ስርአት፣ የህዝብ ለሕዝብ ግንኙነት በማጠናከር የሚያስችሉ ስራዎችን በመስራት ዋናውን የሽግግር ፍትህ ሂደት የማገዝ እና የመደገፍ ሚና ይኖራቸዋል፤
- በኮሚሽኑ የሚቀመጡ መርሆችን መሰረት በማድረግ
  - በሀገራዊ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን የማይከናወኑ ወይም የማይሸፈኑ ጉዳዮችን፣ ወይም
  - ቀለል ያሉ የመብት ጥሰቶች/ግጭቶችን ለመፍታት እንዲቻል ተቋማቱ በእውነት ማፈላለግ፣ በእርቅ ተግባራት፣ ተያያዥ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋሉ፡
- አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ባህላዊ የፍትህ ሥርአቶችን ለመለየት የሚያስችሉ መርሆችና መስፈርቶች በግልፅ ይወጣሉ፤
- ተቋማቱ ከፖለቲካ፣ ከዘር፣ ከሀይማኖት፣ ከፆታ እና ሌሎች አድሏዊ አሰራሮች ነፃ እና ገለልተኛ ሆነው የሚሰሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስርዐት ይቀረፃል፤
- የተቋማቱ አሰራር የሴቶች እና ህፃናትን ተሳትፎ እና መብት እንዲያከብር ተገቢ ስራ ይሰራል።

# 10. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዩች (cross-cutting issues)

- የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና ትግበራ ሂደት አንዱ ገዢ መርህ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ትኩረት መስጠት ነው።
- የሽ/ፍ/ፖ እና ትግበራው ልዩ ትኩረት ለሚሹ (ሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ተፈናቃዮች) ልዩ ፍላጎት/ጥቅም ትኩረት በሚሰጥ አግባብ ይከናወናሉ፡
- ከተጋላጭ የህብ/ብ ክፍሎች አንፃር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡-
    - ፖሊሲውን ለመተገበር የሚወሰዱ የህግ፣ የአሰራር፣ የአደረጃጀት እርምጃዎች የሴቶችን ትርጉም ያለው <u>ተሳትፎ/ውሳኔ ሰጪነት/ተመጣጣኝ ውክልና </u>ያረጋግጣሉ፡
    - ትግበራው በማህበረሰቡ የቀዩ የተዛቡ የስርአተ–ጾታ አመለካከቶችን እና ተጋላጭነታቸውን በዘላቂነት ለመቀነስ በሚያስችል አግባብ ይከናወናል፤
    - የምርመራ/ክስ ሂደቶች ለጾታዊ ጥቃት ሰለባ ሴቶች ለዳግም ጉዳት የማያጋልጡ፣ የስነልቦና/የምክር ድጋፍ የሚያቀርቡ፣ የማገገሚያ አገልግሎት ያካተቱ ይሆናል፡
    - የምርመራ/ክስ፣ እውነት የማፈላለግ/የእርቅ ስራ ሂደቶች የሴቶችን የባህል/የእምነት ልዩነቶች፣ የማህ/ብን ተጽእኗዊ አኗኗር በማየት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ፡
    - በክስ/ምርመራ ወቅት የሚተገበሩ የሥነ-ሥርዓት/የማስረጃ ህጎች ጾታዊ ጥቃት የፈጸሙ አጥፊዎች ተጠያቂነትን ማረጋገጥ በሚያስችሉ መልኩ ይተገበራሉ፤
    - የእውነት ማውጣት ሂደቱ ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ልዩ ትኩረት ይሰጣል፤ የጥቃቶችን ተከታታይነት (pattern) በማጥናት ምክንያቶቹ ይፋ ያወጣል፡
    - የእውነት ማውጣት ሂደቱ በአገር ውስጥ ተፈናቃዮች/ሌሎች ተጋላጭ የህብ/ብ ክፍሎች ላይ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ባካተተ መልኩ ይተገበራል፤

# 10. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዩች (cross-cutting issues)

- በሽግግር ፍትህ ትግበራ ላይ የሚተላለፉ የማህ/ብ ግንዛቤ ትምህርቶች ለሴቶች እና ልጃገረዶች ተደራሽ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ይከናወናሉ፤
- ህጻናትን በተመለከተ ሂደቱ በህገ-መንግስቱ እና በአለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ላይ በተቀመጡ መብቶች መሰረት ይተገበራል፤
- የወንጀል ተጠያቂ ህጻናትን በመለየት ሂደት፣ እንዲሁም በምርመራ፣ ክስ፣ ክርክር እና ውሳኔ አሰጣጥ ለህጻናት ተገቢው ትኩረት ይሰጣል፤ ጥንቃቄም ይደረጋል፤
- ትግበራው የወጣቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ባረጋገጠ መልኩ ይከናወናል፤
- ለአካል ጉዳተኞች እና ለአረጋውያን ተደራሽ እንዲሁም አካታች የሆኑ አሰራሮችን ያካተተ ይሆናል።

# ክፍል ሦስት - የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እና የክትትል እና ድጋፍ ስርዓት

1) የመንግስት አካላት እና ባለድርሻ አካላት ሚና

- በፖሊሲው መሰረት የሽግግር ፍትህ ስራዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማት በርከት ያሉ ናቸው፡
- እነዚህ ተቋማት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ስራቸውን እስኪጀምሩ ድረስ ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት ተግባር በዚህ ፖሊሲ ላይ በግልፅ ሊመላከት ይገባል፡
- በሌላ በኩል በፖሊሲው ተቋቁመው ስራዎች የሚሰሩ ተቋማት በመካከላቸው የሚኖረውን ቅንጅት የሚመራ መዋቅር እና ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት ያስፈልጋሉ፡

የመንግስት አካላት ሚና

ሀ) የፍትህ ሚኒስቴር

- የሽ/ፍ ሂደቱ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር አንፃር የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ይደረጋል፡
- ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን በማመቻቸት እና በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ተግባራትን የሚያከናውኑ አካላትን በመደገፍ የዋና አስተባባሪነት ሚና ይኖረዋል፡
- እንዲቋቋሙ የተመለከቱ ተቋማት ማቋቋሚያ የሕግ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
- የሚቋቋሙ ተቋማት ራሳቸውን ችለው ስራ እስኪጀምሩ ድረስ የውስጥ አሰራር ደንቦችን/መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ ተገቢው ድጋፍ ያደርጋል፤
- በተለያዩ የሽግግር ፍትህ ተቋማት እና አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፤ አጠቃላይ የሽግግር ፍትህ አፈፃፀምን ይከታተላል፤
- ይህን የሚያከናውን ከሚመለከታቸው ተቋማት እና ሲቪል ማህ/ብ ተወካዮች የተውጣጡ አባላት ያሉት አደረጃጀት ይመሰርታል፤

# ክፍል ሦስት - የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እና የክትትል እና ድጋፍ ስርዓት

## ለ) የገንዘብ ሚኒስቴር

- በሀገርአቀፍ ደረጃ የሽግግር ፍትህ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በቂ በጀት ይመድባል፤
- በፈፃሚ ተቋማቱ ማቋቋሚያ ህግ ላይ በሚመለከተው አግባብ በጀት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ልዩ አሰራር ያሳልጣል፤
- ከአለምአቀፍ/ሀገር አቀፍ አጋር አካላት ጋር በቅርበት ይሰራል፤ ሀብት ያሰባስባል፤ የሚገኘውን ድጋፍ ማስተዳደር እና መጠቀም የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

## ሐ) የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን

- የሽግግር ፍትህ ተቋማት ተግባር እንዲሁም የተልዕኳቸውን አስቸኳይነት እና ልዩ ባህርይ ግምት ውስጥ በማስገባት ስራቸውን ለማሳለጥ የሚያስችል የግዢ አፈፃፀም እና የንብረት አወጋገድ ስርዓት እንዲኖራቸው ያደርጋል/ያግዛል፤
- በተቋማቱ ማቋቋሚያ ህግ ላይ በሚመለከተው አግባብ የግዢ ስራዎች የሚፈፀሙበት ልዩ አሰራር ዝግጅት እና አፈፃፀም ያሳልጣል።

## መ) ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

- የሽግግር ፍትህ ተቋማት በማቋቋሚያ ህግ ላይ በሚመለከተው አግባብ የተልዕኳቸውን ልዩ ባህርይ ግምት ውስጥ ያስገባ አደረጃጀት እንዲኖራቸው እገዛ ማድረግ፤
- ተቋማቱ የተሻለ እውቀት/ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎችን ለመቅጠር/ለመመደብ የሚያስችል የደመወዝ እና የጥቅማጥቅም ማዕቀፍ እንዲኖር እገዛ ማድረግ፤

# ክፍል ሦስት - የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እና የክትትል እና ድጋፍ ስርዓት

### ሠ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን

- የሲቪል ማህ/ብ ድርጅቶች ማህበረሰቡን በሽግግር ፍትህ ጉዳይ የማሳወቅ እና የማንቃት ስራ እንዲሰሩ ማስተባበር፤
- የሲቪል ማህ/ ድርጅቶች የሚወክሉት የህ/ብ ክፍል በሽግግር ፍትህ ስርዓት አተገባበር ሂደት በንቃት ይሳተፉ ዘንድ እንዲያበረታቱ ማድረግ፤
- በሽግግር ፍትህ አተገባበር የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማስተባበር።

### ረ) የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች

- የሚቋቋሙ ተቋማት ወይም አደረጃጀቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሰላም እና የፀጥታ ችግር እንዳይገጥማቸው አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፤
- የሽግግር ፍትህ ስርዓት የተለያዩ ክፍሎችን ተግባራዊ ለማድረግ በልዩ ሁኔታ ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህን ማከናወን።

### ሰ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

- የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ <u>የሚያስችሉ ሕጎችን ቅድሚያ እና ትኩረት በመስጠት ያፀድቃል</u>፤
- የሚቋቋሙ ተቋማት <u>ኮምሽነሮች እና ዳኞች ሹመት ግልፅ በሆነ እና የህዝብን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ ሂደት</u> እንዲከናወን ያደርጋል፤
- የሽግግር ፍትህ አጠቃላይ ስርአት የህዝብን አመኔታን ባረጋገጠ መንገድ፣ በታቀደው አግባብ እየተተገበረ <u>ስለመሆኑ ክትትል ያደርጋል፡ በጀት ያፀድቃል</u>፤

# ክፍል ሦስት - የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እና የክትትል እና ድጋፍ ስርዓት

### ሸ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

- ለሚቋቋመው ልዩ ፍርድ ቤት ምቹ የስራ ቦታ፣ የአሰራር ሥርዓት እና የተሻለ የሰው ሀይል እንዲኖረው አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
- በልዩ ፍርድ ቤት እና በመደበኛ ፍርድ ቤቶች መካከል ልምድ ለማጋራት የሚያስችል ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

### 2) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሚና

- ሁሉም የህብ/ብ ክፍሎች ስለ ሽግግር ፍትህ ሥርዓት/ሂደት ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማስገንዘብ፣ አገራዊ ንቅናቄ በመፍጠር በባለቤትነት ስሜት እንዲሳተፍ ይሰራሉ፡፡
- በአተገባበር ወቅት በቀጥታ እንዲሳተፉ፣ ሂደቱን እንዲደግፉ እንደአግባብነቱም የሂደቱን ውስን ክፍሎች በሙሉ ሀላፊነት የሚያስፈፅሙበት አውድ ይፈጠራል፡፡
- ዓለማቀፍ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም እንደአግባብነቱ ከሀገርአቀፍ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ወይም በተናጠል
  - የህዝብ ባለቤትነት/አገር መሪነት መርህን በሚያከብር አውድ በሂደቱ ትግበራ የሚሳተፉበት ስርአት ይዘረጋል፤
  - ስርአቱን በፋይናንስ፣ በቴክኒክ እና ሌሎች መንገዶች የሚደግፉበት አሰራር ይመሰረታል፡፡

## 3) የፖሊሲው አፈፃፀም፡ ክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት

- ይህ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በሚፈለገው አግባብ ተግባራዊ እንዲሆን ራሱን የቻለ የክትትል እና ድጋፍ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡
- በፖሊሲው የተመለከቱ ተቋማት ስራቸውን እስኪጀምሩ፣ እንዲሁም ስራቸውን ከጀመሩ በኋላ ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የተቀናጀ እና የተናበበ ድጋፍ እና ክትትል የሚካሄድበት ስርአት መኖር አለበት፡
- ለፍትህ ሚኒስቴር የተሰጠው ቅንጅታዊ አሰራር የመመስረት/የባለ–ብዙ ተቋማት እና ሲቪል ማህ/ ድርጅቶች አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ፥
  - ፖሊሲው ወደ መሬት ወርዶ ተግባራዊ የሚሆንበትን ዝርዝር አካሄድ የሚመራ 'የፖሊሲ አፈፃፀም ፍኖተ ካርታ' ይዘጋጃል፡
  - ፍኖተ-ካርታው ፖሊሲው ከጸደቀ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት በዝርዝር ምን እንደሆኑ፣ መቼ እንደሚከናወኑ፣ በማን - ያመላክታል፡
  - የፍትህ ሚኒስቴር የሚያቋቁመው የክትትል አደረጃጀት ይህን ፖሊሲ እና ፍኖተ ካርታውን መነሻ በማድረግ የየተቋማቱ ተግባራት በአግባቡ እና ቅንጅታዊ አሰራርን መሰረት በማድረግ ይፈፀሙ ዘንድ በቋሚነት የክትትል እና ድጋፍ ስራ የሚሰራ ይሆናል።